# የሥዓተ-ፆታ ግንዛቤ ለማሳደግ የተዘጋጀ

## የስልጠና ማንዋል

Training manual for

## Gender Awareness Raising

አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮች ገበያ ተኮር የአትክልት/ፍራፍሬ ልማት አጋዥ
ፕሮጀክት (ኢትዮ-ሸፕ)

# ማውጫ


1. ስልጠናው ለማዘጋጀት የሚጠቅሙ መሠረታዊ ነጥቦች ....3
2. መግቢያ ....4
   2.1. ደረጃ 1. የሥርዓተ-ፆታ እና ጾታ ጽንሰ-ሀሳብ መረዳት....4
3. የሥርዐተ-ፆታ ትንታኔ....6
   3.1. ሰነድ/ ቅጽ 1፣ ደረጃ 2. በቤተሰብ ደረጃ (በወንዶችና በሴቶች መካከል) የሥራ ድርሻና ኃላፊነቶች መለየት....6
4. የሥርዓተ-ፆታ ትንታኔ ሰነድ 3 ....8
   *4.1. ደረጃ 3. ዋና ዓላማው በገጠሩ ኣርሶ ኣደሮች ወንዶችን፣ ሴቶችን ወንዶች ልጆችንና ልጃገረዶችን ጨምሮ እለት ተእለት የሥራ ጫና ለማወቅና እያንዳንዱ ሥራ ለመከወን የሚፈጀው ጊዜ ለመገመት ይረዳል።....8*
5. የሥርዓተ-ፆታ ትንተና- ክፍል 3....10
   5.1. ደረጃ 4. ሥርዓተ-ፆታን መሠረት ያደረገ የሀብት ተደርራሽነት እና መቆጣጠር ትንተና....10
6. ታርክ ፆታዊ ጉዳዮች በተመለከት ከስነ-ጾታ ጋር የተያያዙ ታሪኮች....12
7. የ1ኛው ቀን ማጠቃላያ....13
   7.1. ደረጃ 5. የማጠቃለያ ክፍል ....13
8. የሥርዐተ-ፆታ ትንታኔ መተግበርያ 4 ....14
   8.1. ደረጃ 6. የሥርዐተ-ጾታ ድርጊት-መርሀ ግብር ማዘጋጀችት ....14

የስልጠና ፕሮግራም የጊዜ ሰሌዳ

**1ኛ ቀን**

| ተፈላጊ ሰዓት (የሚወስደው ጊዜ) | ተግባራት |
|---|---|
| 9:00 – 9:30 | መግቢያ፥- ሥርዐተ-ፆታ እና ጾታ ልዩነት መረዳት |
| 9:30 – 10:15 | ሰነድ/ ቅጽ 1፣ የስራ ድርሻና ሀላፊነት |
| 10:15 – 10:45 | ሰነድ/ ቅጽ 2፣ ዕለታዊ ስራ ክንውን የጊዜ ሰሌዳ |
| 10:45 – 11:15 | ሰነድ 3: ሀብትን የመገልገልና የማግኘትና የመቆጣጠር ቁጥጥር ሓላፊነት |
| 11:15 – 11:30 | ውይይት/ማጠቃለያ |

**2ኛ ቀን**

| ተፈላጊ ሰዓት የሚወስደው ጊዜ | ተግባራት |
|---|---|
| 9:00 – 10:15 | ማጠቃለያ/ ሰንድ 4: ሥርዓተ-ፆታ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት |

## 1. <u>ስልጠናው ለማዘጋጀት የሚጠቅሙ መሠረታዊ ነጥቦች</u>

ቅድመ ዝግጅት | 1ኛ ቀን | 2ኛ ቀን

- ሥልጠናው ከመዘጋጀቱ በፊት ባልና ሚስት አርሶ አደሮች በጋራ የስልጠናው ተሳታፊ እንዲሆኑ ማነሳሳትና ማረጋገጥ፣
- በቡድን ውይይት ክፍለ ጊዜ ሴቶችና ወንዶች **በአንድ ላይ በማስቀመጥ** ሀሳባቸውን እርስ በርስ **በነጻነት** አንዲለዋወጡ ማረጋገጥ፣
- **አስተባባሪው**/ዋ (የሥርዓተ ፆታ ባለሙያ ወይም የልማት ሠራተኛ) የሁሉንም አርሶ አደሮች **ንቁ ተሳትፎ** ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል፣
- አርሶ አደሮች የእያንዳንዱ ተሳታፊ ድርጊት ሂደትን መከታተል፣ ለምን ዓላማ መደረጉን መረዳታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣
- በወንድና በሴት መካከል ያለ የሥራ ጫናና ሃላፊነት በእኩል ቢዳረስ ያለውን ጥቅም ግንዛቤን በማስረፅ የሴቶችን የሥራ ጫና በመቀነስ ዙሪያ ተሳታፊዎች እንደተረዱ መረዳታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

**ግንዛቤ ማስጨበጫ ቅስቀሳ ግንዛቤአቸው ከተሻሻል** በኋላ፣-

- ስልጠናው የወንዶችን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ የሴቶች ከባድ የሥራ ጫና መንስኤ በእርሻ ስራ ሳይወሰን ቤተሰባቸውን ለመንከባከብ የሚከናውኑባቸው የሚያከናውኗቸው የቤት ሥራዎችን ይጨምራል፣
- ስልጠናው የወንዶች ግንዛቤ ከፍ በማድረግ ባሎች ሚስቶቻቸውን በማገዝ የሴቶችን በእርሻ ተግባራት ይበልጥ ውጤታማ አንዲሆኑ ያስችላል፣
- ሴቶች ለገቢ ማስገኛ ስራ የሚሆን ተጨማሪ ግዜ ስለሚያገኙ የቤተሰቡን ገቢ ያሳድጋል።



በስልጠና ላይ የተወሰኑትን ኣርሶ ኣደሮች በውይይት ሰዓት ደካማ ተሳትፎ አንደሚያሳዩ ይታወቃል። በዚህ ሁኔታ የስልጠናው አስተባባሪው/ዋ የተሳታፊዎች አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይገባል።

ሥልጠና ዝግጅት | 1ኛ ቀን | 2ኛ ቀን

2. መግቢያ

2.1. ደረጃ 1. የሥርዓተ-ፆታ እና ጾታ ጽንሰ-ሀሳብ መረዳት

**ዓላማ**

በሥርዓተ-ፆታ እና በጾታ መካከል ያለው ልዩነት ለመረዳት

**የሚፈጀው ጊዜ**

30 ደቂቃ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች**

ተገላጭ ቻርት ◆ ማስመሪያ ◆የመፃፊያ ማርከር

**2.2. የስልጠናውን ትግበራ ሂደት**

| ሂደት | ተግባራት/ ድርጊት |
|---|---|
| ደረጃ 1 | የእንኳን ደህና መጣችሁና የእርስ በርስ ትውውቅ፣ የሥርዐተ-ፆታ ግንዛቤን ለማሳደግ የስልጠናው ዓላማና ያስፈለገበት ምክንያት ለተሳታፊዎች ገለጻ ማድረግ። |
| ደረጃ 2 | ተሳታፊዎችን ስለ ሥርዐተ-ፆታ የሰሙት ነገር ካለ መጠየቅና መልሳቸውንም በተቻለ መጠን ሙሉ በሙሉ መመዝገብ ያስፈልጋል። |
| ደረጃ 3 | ➢ ሁሉም ተሳታፊዎች ምንም የሰሙት ነገር ከሌለ፣ ወደ ድርጊት 4 ይቀጥሉ<br>➢ ከተሳታፊዎች መካከል የሰሙት ነገር ካለ ግን የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አንድ በአንድ ለተሳታፊዎች አንብቡላቸው።<br>➢ በመቀጠልም እያንዳንዱ አረፍተ ነገር የሚገልጸው "ሥርዐተ-ፆታ" አልያም "ጾታ" መሆኑ መጠየቅ። በቅድሚያ "ሥርዐተ-ፆታ" የሚሉትን እጃቸምን እንድያወጡ መጠየቅ፣ በማስከተል ""ጾታ" ነው የሚሉትን እጃቸውን አንድያወጡ እድል ይሰጣቸው።<br>➢ ተገላጭ ቻርት ላይ "ሥርዐተ-ፆታ" እና "ጾታ" ነው የሚሉትን ቁጥራቸው መጻፍ፣<br>➢ በተቻለ መጠን የያንዳንዱ ሀሳብ ሙሉ በሙሉ መመዝገብ ያስፈልጋል፣ ይህ ተግባር ከታች የተዘረዘሩትን ስድስት(6) አረፍተ-ነግሮች ፍጻሜ ድረስ ይቀጥላል።<br>*(1) ሴቶች ልጅ ይወልዳሉ፡ ወንዶች መውለድ ኣይችሉም (ጾታ)*<br>*(2) ወንዶች ጠንካራ ሲሆኑ ሴቶች ግን ለስላሳ ናቸው (ስርዓተ- ጾታ)*<br>*(3) ሴቶች ጡት ያጠባሉ፣ ወንዶች ጡጦ ያጠባሉ (ጾታ)*<br>*(4) የቤት ሥራዎችን ማከናወን የሴቶች ሃላፊነት ነው (ስርዓተ-ጾታ)*<br>*(5) የቤተሰብ ንሮ ማሸንፍ የወንዶች ሃላፊነት/ድርሻ ነው (ስርዓተ-ጾታ)*<br>*(6) ሴቶች በህዝባዊ ስፍራዎች መናገር የለባቸውም (ስርዓተ-ጾታ)*<br>ስድስተኛ (6) ዓረፍተ-ነገር ከተነበበ ከላይ የተሰጡት መልሶች አንብቡላቸው። ከላይ የተገለፁት ሶስት የቤተሰብ አይነቶች ለምሳሌነት ነው። በቁልፍ አስረጂዎች ቃለ መጠይቅ ወቅት ሌሎች የቤተሰብ አይነቶች ሊገለፁ ይችላሉ ። |
| ደረጃ 4 | የአሰልጣኝ ማብራሪያ፡ "ፆታ" ማለት በተፈጥሮ የሚገኝ እና ሁላዊ መሆኑ እንዲሁም በጊዜ ሂደት የማይቀየር መሆኑ ማብራራት፥ በተመሳሳይ መልኩ "ሥርዐተ-ፆታ" ከማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ጋር የተሳሰረ በወንዶችና ሴቶች መካከል ያለውን የተዛቡ የአመለካከት ድምዳሜዎች ያመላክታል፣ በጊዜ ሂደት የሚቀየር መስተጋበር መሆኑ ማብራራት ያስፈልጋል። |

| | |
|---|---|
| ደረጃ 5 | የስልጠናው ተሳታፊዎች በፆታና **በ**ሥርዓተ-ፆታ መካከል ያለውን ልዩነት በትክክል መረዳታቸውን ካረጋገጥን በኋላ፣ ከላይ ወደተዘረዘሩት ስድስት (6) ዐረፍተ-ነገሮች የሚያመለክቱት የስልጠናው ተሳታፊዎችን "ፆታ" ወይም "ሥርዐተ-ጾታ" መሆኑ እንዲያስረዱን መጠየቅና መረዳት እንዲረዱ ማድርግ፡፡ |
| ደረጃ 6 | የስልጠናው ተሳታፊዎች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ከዚህ በፊት የወንዶች የስራ ድርሻዎች ብቻ የሚታውቁ አሁን ግን በወንዶችና በሴቶች የሚከናወኑ ካሉ የስልጠና ተሳታፊዎችን እንዲያስረዱን መጠየቅ፥ በአንጻሩ ግን ከዚህ በፊት ለሴቶች ብቻ የተተዉ የስራ ድርሻዎች አሁን ግን በወንዶችና በሴቶች የሚከናወኑ ስራዎች ካሉ ለስልጠና ተሳታፊዎችን እንዲያስረዱን መጠየቅና እንዲያብራሩ ማድርግ። በመጨረሻ ምየስልጠና ተሳታፊዎች "ሥርዓተ-ጾታ" በጊዜ ሂደት በሚኖሩበት ህብረተሰብ ጨምሮ የሚቀየር መስተጋብር መሆኑን መገንዘባቸው ማረጋገጥ/ማብራራት ያስፈልጋል። |



**የተሳታፊዎችን ግንዛቤ የምናረጋግጠበት ነጥቦች፥-**

- የስልጠና ተሳታፊ አርሶ አደሮች በሥርዐተ-ፆታ እና ጾታ መካከል ያለው ልዩነት ተረድተዋል።
- ጾታ ሊለወጥ ኣይችልም፣
- ሥርዓተ-ፆታ በግዜ ሂደት ሊለወጥ ይችላል ።

ሥልጠና ዝግጅት > 1ኛ ቀን > 2ኛ ቀን

3. የሥርዐተ-ፆታ ትንታኔ

**ሥርዓተ-ፆታን መሠረት ያደረገ የሥራ ክፍፍል**

3.1. ሰነድ/ ቅጽ 1፣ ደረጃ 2. በቤተሰብ ደረጃ (በወንዶችና በሴቶች መካከል) የሥራ ድርሻና ኃላፊነቶች መለየት

**የስልጠናው ዓላማ**

የስልጠናው ተሳታፊዎች በቤተሰብ ደረጃ በወንዶችና በሴቶች መካከል የስራ ድርሻዎችና ኃላፊነቶች መለየትና ማስረዳት

**የሚፈጀው ጊዜ**

45 ደቂቃ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች**

ተገላጭ ቻርት፣ መፃፊያ ማርከር፣ እስክርቢቶ መፃፊያ ማርከር

**3.2. በስልጠና ጊዜ ደረጃ በደረጃ የሚሠሩ ተግባራት**

<table>
<tr><th>ቅደም ተከተል</th><th>ዝርዝር ተግባራት</th></tr>
<tr><td>ደረጃ 1</td><td>ቀዳሚ ተግባር፡- "የአምራችነት ሚና" እና "የስነ-ተዋልዶ ሚና" ("የአምራችነት ሚና") ሰንጠረዥ በማየት ሌላ ሰንጠረዥ በተገላጭ ቻርት ለሁሉም በግልጽ በሚታይ መልኩ መሳል።</td></tr>
<tr><td>ደረጃ 2</td><td>በ"አምራችነት ሚና" ላይ በማመላከት የስልጠናው ተሳታፊዎችን በቀበሌአቸው ውስጥ የሚመረቱና ለገበያ የሚቀርቡ ዋና ዋና የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች እንዲያስረዱን መጠየቅ፣ በመቀጠል ከተዘረዘሩት መካከል ከሁሉም በላይ በተሻለ ጠቃሚ የሆነውን አንዲለዩ በመጠየቅ መረዳት።</td></tr>
<tr><td>ደረጃ 3</td><td>የስልጠናው ተሳታፊዎች አባላት ከተመረጡትን ምርቶች አንጻር በማገናዘብ የማምረት፣ የግብይት እና ገቢን መቆጣጠር የመሳሰሉት ከ8-10 ቁልፍ ተግባራት እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ እያንዳንዱ ተግባር በሰንጠረዡ ኮለም(2) ውስጥ መመዝገብ። በስተመጨረሻ የሚጻፉት ሁለት ተግባራት ለግብይት ተግባር እና ገቢን ለመቆጣጠር የተመደቡ ናቸው።<br><br>ሰንጠረዥ: የአምራችነት ሚና
<table>
<tr><th>ተራ ቁጥር</th><th>ተግባራት</th><th>ወንዶች</th><th>ሴቶች</th></tr>
<tr><td>1</td><td>የችግኝ ማፍያ መደብ ማዘጋጀት</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>2</td><td>የአትክልት ዘር መዝራት</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>3</td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>4</td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>5</td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>6</td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>7</td><td>ግብይት ማከናወን</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>8</td><td>የቤተሰብ ገቢ መቆጣጠር</td><td></td><td></td></tr>
</table>
የመጨረሻዎቹ 2 ኮለሞችቋሚ ናቸው! ማን ሰብሎችን ገበያ ላይ እንደሚሸጥ እና ማን ገቢን እንደሚቆጣጠር ውይይት አድርጉ!</td></tr>
<tr><td>ደረጃ 4</td><td>በ"ማህበራዊ ድርሻዎች" "በስነ-ተዋልዶ ሚና" ላይ በማመልከት፣ ከስር ከታች የተዘረዘሩትን የቤተሰብ እንክብካቤንና የቤት ውስጥ ዋና ስራዎች በመጥቀስ የእነሱ ሚናና ተግባራት የተረዱትን እንዲያብራሩ የስልጠናው ተሳታፊዎችን ምን እንደሆነና በመጠየቅ መረዳት/ለተሳታፊዎች እንዲያካፍሉ ማድረግ።</td></tr>
</table>

| | |
|---|---|
| **ደረጃ 5** | በመቀጠልም የስልጠናው ተሳታፊዎችን በወንድና የሴት ቡድን መክፈል። ለሁለቱም ቡድን **"የአምራችነት ሚና"** እና **"የማህበራዊ ሚና"** የተጻፈባቸው ቅጾች ይሰጣቸው። ከተሳታፊዎች መካከል አንድ ሰው ለአንድ ቡድን በፍቃደኝነት ልምምዱን እንዲያስተባብር መሰየም። |
| **ደረጃ 6** | እያንዳንዱ አስተባባሪ (ቡድን መሪ) የትኞቹ ተግባራት በወንዶች ወይም በሴቶች የሚሰሩ መሆናቸውን የቡድኑ አባላትን መጠየቅ አለበት። መልሱ 'ወንዶች' ወይ 'ሴቶች' ከሆነ አንዴ ብቻ በጾታው ትይዩ ሳጥን የቲክ ምልክት ማድረግ፣ 'ሁለቱንም በእኩል ይሳተፋሉ ከሆነ በሁለቱንም ትይዩ አንዴ የቲክ ምርልክት (tick) ማድረግ። ባንጻሩ ሁለቱንም ተሳትፎ የላቸውም ከሆነ ምንም ምርልክት አለማድረግ። |

**<u>የአምራችነት ሚና</u>**

| ተግባራት | ወንዶች | ሴቶች |
|---|---|---|
| የችግኝ መደብ ማዘጋጀት | | |
| ግብአት መግዛት | | |
| ልብስ ማጠብ | | |
| ችግኝ ማዛዋር | | |
| ማረም | | |
| ማዳበሪያ መጠቀም ማድረግ | | |
| ምርት መሰብሰብ/ ማጨድ | | |
| ምርት መሸጥ | | |
| ገቢን መቆጣጠር | | |

**<u>የስነ-ተዋልዶና ማህበራዊ ሚናዎች</u>**

| ተግባራት | ወንዶች | ሴቶች |
|---|---|---|
| ምግብ ማብሰል | | |
| ልብስ ማጠብ | | |
| ውሃ መቅዳት | | |
| የማገዶ እንጨት ማምጣት | | |
| ልጆች መንከባከብ | | |
| ታማሚን መንከባከብ | | |
| ማስፈጨት/ | | |
| ቤት መገንባት/ መጠገን | | |
| የቤተሰብ ደህንነት የመቆጣጠር ሚና | | |

እያንዳንዱ ተግባር የመከወን እለታዊ ሃላፊነት የማን እንደሆነ ለሰልጣኞቹ ቡድን አባላትን መጠይቅ ጠይቁ። አልፎ አልፎ ብቻ የሚሰሩት ከሆነ ግን ምንም ምልክት ኣታድርጉ።

| | |
|---|---|
| **ደረጃ 7** | እሁን ወደ ማጠቃለያ ክፍለ-ጊዜ ደርሰናል። የእያንዳንዱ ቡድን የሰራው በመጠይቅ የአምራችነት ተግባራት በተመለከተ የተኞቹ ተግባራት በወንዶች እና በሴቶች መካከል እንዴት እንደተከፋፈሉ በጋራ ውይይት ማድረግ ሁለቱ ቡድኖች የሰሩትን ማነጻጸር |



**<u>ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነጥቦች፡-</u>**

- የሴቶችን ከፍተኛው የስራ ተሳትፎ ማህበራዊ ኃላፊነት ማለትም ከባድና አምራች ባልሆኑ የቤትና የቤተሰብ አባላት ጥበቃና እንክብካቤን ጋር የተቆራኘ ነው፥ ይህም በገብያና በግብይትና ገቢን መቆጣጠር ያላቸው ተሳትፎ እነስተኛ ስለሚያደርገው የሴቶች በግብርና ተሳትፎ (በምርት እና በግብይት ላይ) ዝቅተኛ ሊያደርገው ይችላል።
- በማህበራዊ ኃላፊነቶች ረገድ ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ የሴቶች ኃላፊነት ነው ሊባል ይቻላል።

**ማገናዘብያ ነጥቦች፡-**

- የሴቶች በሆርቲካልቸር በአትክልት ሰብሎች ምርት ማምረት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያበረክታሉ፡፡
- ሴቶች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኃላፊነቶች በመወጣት ከፍተኛ ጫና ይሸከማሉ። ወንዶች ደግሞ ከሴቶች ሲነጻጸር በእጅጉ ያነሰ ጫና ይኖርባቸዋል።

ሥልጠና ዝግጅት > 1ኛ ቀን > 2ኛ ቀን

4. የሥርዓተ-ፆታ ትንታኔ ሰነድ 3

**ዕለታዊ የስራ ክንውን የጊዜ ሰሌዳ**

*4.1. ደረጃ 3. ዋና ዓላማው በገጠሩ አርሶ አደሮች ወንዶችን፣ ሴቶችን ወንዶች ልጆችንና ልጃገረዶችን ጨምሮ እለት ተእለት የሥራ ጫና ለማወቅና እያንዳንዱ ሥራ ለመከወን የሚፈጀው ጊዜ ለመገመት ይረዳል።*

**የስልጠናው አላማ፡-**

ተሳታፊዎች በቤተሰብ ደረጃ የወንዱና የሴቱ የሥራ ድርሻና ኃላፊነቶች መረዳት

**ለስልጠናው የሚያስፈልግ ግዜ፡-**

30 ደቂቃ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች**

ተገላጭ ቻርት* ማስመሪያ * መፃፊያ ማርከር

4.2. ደረጃ በደረጃ የሚሰሩ ተግባራት

| **ቅደም ተከተል** | **ዝርዝር ተግባራት** |
|---|---|
| ደረጃ 1 | ወንድና ሴቶች ተሳታፊዎች ለሁለት(2) በመከፈል ቡድኖችን እንዲመሰርቱ ማድረግ።<br>**“ዕለታዊ የስራ ክንውን መቁጠሪያ”** ሰንጠረዥ በመጠቀም የሥራ ድርሻቸውን በሰንጠረዥ ላይ እንዲጽፉ ይደረጋል።<br>አስተባባሪው/ዋ ከተሳታፊዎች ከእያንዳንዱ ቡድን ኣንድ ሰው መርጦ/ጣ የቡድን ሥራው እንዲረዱ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡ |
| ደረጃ 2 | በመስኖ ወቅት የስራ ቀን እንዲመርጡ በማድረግ በመውሰድ ለያንዳንዱ ቡድን የወንዶችና የሴቶች የሥራ ድርሻዎችና ሃላፊነቶች በተመለከተ ጥያቄ በመጠየቅ ማብራሪያና ይሰጣሉ። መብት አላቸው፣ |

**የሴቶች እለታዊ ስራ በገጠር ህብረተሰብ**

| ሰአት | ተግባሮች |
|---|---|
| ከነጋቱ 11 ሰዓት | ከእንቅልፍ መንቃት / ወተት ማለብ |
| ከጠዋቱ 1 ሰዓት | ቁርስ ማዘጋጀት |
| ከጠዋቱ2 ሰዓት | በአማድ አፈር ማከም |
| ከጠዋቱ 3ሰዓት | በማሳ መስራት |
| ከቀኑ 6 ሰዓት | ምሳ ማዘጋጀት |
| ከቀኑ 7ሰዓት | የምግብ እቃ ማጠብ/ ከብቶች መመገብ/ ውሃ መቅዳት/ እንጨት መልቀም/ ወተት ማለብ |
| ከቀኑ 11 ሰዓት | እራት ማዘጋጀት |
| ከቀኑ 12 ሰዓት | ከብት ማሰማራት / ልጆች ማጠብ |

**የወንዶች እለታዊ ስራ በገጠር ህብረተሰብ**

| ሰዐት | ተግባሮች |
|---|---|
| ከነጋቱ 11 ሰዓት | የቤትና የቤተሰብ አባላት ደህንነት ፍተሻ |
| ከጠዋቱ12 ሰዓት | ከእንቅልፍ መንቃት / ደህንነት ፍተሻ |
| ከጠዋቱ1:30 ሰዓት | ቁርስ መመገብ |
| ከጠዋቱ 2 ሰዓት | የስራ ስምሪት መስጠት |
| ከጠዋቱ 3 ሰዓት | በማሳ መስራት |
| ከቀኑ 7 ሰዓት | ምሳ መመገብ እረፍት |
| ከቀኑ 10 ሰዓት | ጓደኞች ማግኘት |
| ከምሽቱ 1 ሰዓት | ለእራት እረፍት |
| ከሌሊቱ 4 ሰዓት | ወደ መኝታ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ከምሽቱ 2 ሰዓት | እራት | |
| | ከምሽቱ 3 ሰዓት | የምግብ እቃ ማጠብ | |
| | ከምሽቱ4 ሰዓት | ገላ መታጠብ | |
| | ከምሽቱ 5 ሰዓት | ወደ መኝታ | |

**ስልጠናው በማስፈጸም ሂደት ጠቃሚ ቅምሻ/ጥቆማዎች፥ እየተተገበረ /እየሆነ ሰላልው ፍንጭ**

- ሴቶች ቀን ሙሉ በስራ የሚጠመዱ ሲሆን ወንዶች ግን ለእረፍትንና ለመዝናናት የሚተርፍ ጊዜ አላቸው
- ሴቶች ለስልጠና የሚተርፍ ጊዜ አይኖራቸውም እንዲሁም ተጨማሪ ጊዜ ሰብልን ለማምረት ላይኖራቸው ይችላል።

**ማገናዘብያ ነጥቦች፡-**

- በባድ የስራ ጫና ምክንያት ሴቶች በስልጠና መሳተፍ ሊገታቸውና ሰብል ለማምረት ጊዜ ላይኖራቸው ይችላል።
- ወንዶች በእርሻ ሰራ የሚያጠፉት ጊዜ ኢምንት ነው ሊባል ይችላል

ሥልጠና ዝግጅት > 1ኛ ቀን > 2ኛ ቀን

5. የሥርዓተ-ፆታ ትንተና- ክፍል 3

**በሀብት የመገልገልና ሃብት ይማግኘትና የመቆጣጠር**

5.1. ደረጃ 4. ሥርዓተ-ፆታን መሠረት ያደረገ የሀብት ተደርራሽነት እና መቆጣጠር ትንተና

**የስልጠናው አላማ፡-**

በቤተሰብ ደረጃ ሴቶች በባሎቻቸው (በወንዶችና በሴቶች መካከል) ማን ምን ዓይነት የሀበት ባለቤትነት ተደርራሽነት እና የመቆጣጠር በዋናነት ውሳኔ ሰጪው ማንው? በሥርዓተ-ፆታን መሠረት በቤተሰብ የሚያስከትሉትን አድሎአዊ የሙብትና የስልጣ ለዩነት ካለ

**ሥልጠናው የሚወስደው ጊዜ፡-**

30 ደቂቃ

**የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፡-**

ተገላጭ ቻርት፥ ማስመሪያ ፥ መፃፊያ ማርከር

## 5.2. ደረጃ በደረጃ የሚሠሩ ተግባራት

| **ሂደት** | **ዋና ዋና ተግባሮች** |
|---|---|
| ደረጃ 1 | ቀጥሎ የተመለከተው ከታች ያለው ሰንጠረዥ በመከተል በተገላጭ ቻርት ላይ "የሀብት ባለተደራሽነት ባለቤትነት" እና "የሀብት መቆጣጠር" ("Access to Resources" and "Control of Resources") የሚያሳይ ሰንጠረዥ ለሁሉም ተሳታፊ በግልጽ በሚታይ መልኩ ጻፊ/ጻፍ። በመቀጠል የቃላቶች ትጉም ማለትም ሀብት፣ ተደራሽነት (Access)፣ መቆጣጠር (Control) ምን ማለት እንደሆነ ማብራራት፡፡<br>- **ሀብት**:- አርሶ አደሮች የያዙትና/ የሚጠቀሙት ማንኛውም ጥሪት፡ መሬት፡ የእርሻ መሳሪያዎች፣ ሰብሎች፣ የቤት እንስሳት፣ ወዘተ ያካትታል፡፡<br>- **ተደራሽነት ባለቤትነት**:-ሃብቱን ለመጠቀም ያለው እደል ሙብት፡፡<br>- **መቆጣጠር** :- እያንዳንዱ ሀብት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በዋናነት ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ሙብት ያለው ማነው? ማን ይጠቀምበታል? መቾ መሸጥ አለበት ወዘተ የሚወስነው ማወቅን ይመለከታል፡፡ |
| ደረጃ 2 | ቅድሚያ "የሃብት ተደራሽነት ባለቤትነት" ሰንጠረዥ ላይ በማመላከት፣ ከስሩ የዘረዘሩትን የቤተሰብ የሀብት አይነቶች በተመለከተ የስልጠናው ተሰታፊ አርሶ አደሮች ቡድን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው የአትክትና ሰብሎች እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ በሰንጠረዡ ክፍት መስመር መመዝገብ፡፡<br>በማስከተል ለስልጠናው ተሰታፊ ቡድን አባላት ከተዘረዘሩት የሀብት አይነቶች <u>ያልተካተቱ</u> ነገር ግን ለቤተሰባቸው ገቢ ምንጭነት በጣም ወሳኝ የሆኑ ሁለት ሀብቶች እንዲጠቅሱ መጠየቅና መመዝገብ፡፡<br>ቀጥሎ በ"የሀብት **መቆጣጠር**" ርእስ የተዘጋጁ ሰንጠረገች ሶስት (3) ቅጅ ማዘጋጀት<br>***ሥርዓት-ፆታን መሠረት ያደረገ የሀበት ተደራሽነትና ባለቤትነትና መቆጣጠር*** |

| ሀብት/ አገልግሎት | መጠቀም | | መቆጣጠር | |
|---|---|---|---|---|
| | ወንዶች | ሴቶች | ወንዶች | ሴቶች |
| መሬት | ✓ | ✓ | ✓✓ | |
| የእርሻ መሳርያ | ✓ | ✓ | ✓✓ | |
| የወተት ላም | ✓ | ✓ | ✓✓ | ✓ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዶሮ እርባታ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓✓ |
| ስልጠና | ✓ | ✓ | ✓✓ | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

የስልጠናው ተሳታፊ ቡድን አባላት ለቤተሰባቸው ገቢ ምንጭነት በጣም ወሳኝ የሆኑ 3 ሀብቶች ይወስናሉ። አንዱ ከአትክልት ሰብል ጋር የተያያዘ ሲሆን ሁለት ደግም ከማነኛውም የገቢ ምንጭነት የሚውል ይሆናል።

| | |
|---|---|
| ደረጃ 3 | የስልጠናው ተሳታፊዎች በጾታቸው ለሁለት ቡድን መከፈል። ለእያንዳንዱ ቡድን “የሀብት ባለቤትነት ተደራሽነት” እና “የሀብት መቆጣጠር” ቅጾች ማደል። ከተሳታፊዎች መካከል እንድ ሰው ለአንድ ቡድን በፍቃደኝነት በመሰየም ልምምዱን አንዲያስተባብር ማድረግ። |
| ደረጃ 4 | እያንዳንዱ ቡድን መሪ ለቡድኑ አባላት ‘ማን- ወንዶች ወይስ ሴቶች - የመጠቀም እድል አለው’ በማለት ትጠይቃለች ። መልሱ ‘ወንዶች’ ወይ ‘ሴቶች’ ከሆነ አንዴ ብቻ በጾታው ትይዩ የቲክ ሳጥን ምልክት ማድረግ፣ መልሱ ‘ሁለቱንም በእኩልነት ከሆነ በሁለቱንም ትይዩ አንድ አንድ ጊዜ ምርልክት (tick) ማድረግ። ባንጻሩ ሁለቱንም ተደራሽንት የላቸውም ከሆነ ምንም ምርልክት ኣለማድረግ። |
| ደረጃ 5 | ቅጾቹ በመሙላት ሂደት መጀመርያ “የሃብት ተደራሽነት” ሰንጠረዥ ከጨረሱ በኋላ ወደ “ሀብት መቆጣጠር” ሰንጠረዥ ይቀጥሉ ። ቡድን መሪዋ ለቡድኑ አባላት ከተዘረዘሩት ሀብቶች አንድ በአንድ በመጥቀስ ‘ማን ነው- ወንዶች ወይስ ሴቶች - ይህ ሃብት የመቆጣጠር ስልጣን ያለው? በማለት ትጠይቃለች። ይህ ተግባር እስከ ዝርዝሩ መጨረሻ ድረስ ይቀጥላል። |
| ደረጃ 6 | ወደ ማጠቃለያ ውይይት ተመለሱ። የእያንዳንዱ ቡድን የሰራው በማነጻጸር የትኞቹ - ወንዶች ወይስ ሴቶች- የመጠቀም መብት አንዲሁም የትኞቹ የመቆጣጠር ስልጣን መብት እንደተለያዩ እንዳላቸው ውይይት ማድረግ። |

**ታሳቢ የሚደረጉ ነጥቡች፡-**

- ሴቶች የቤተሰብ የሀብት የመጠቀም መብት ቢኖራቸውም ሀብቱን የመቆጣጠር ስልጣን ግን አናሳ ነው ። በተቃራኒው ግን ወንዶች ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ያለውን ሀብት ይቆጣጠራሉ።
- ማንም ሰው በማይቆጣጠረው ሀብት ላይ ውሳኔ መስጠት አይችልም።
- በኣንድ ቤተሰብ ገቢ ወሳኝ ሚና ያላቸው ሀብቶች በተወሰኑ የቤተሰቡ አባላት በብቸኝነት የተቆጣጠሩት ከሆነ በቤተሰቡ ኢኮኖሚ አሉታዊ ተጽእኖ የማድረስ እድሉ ከፍተኛ ነው።

**ቁልፍ የግንዛቤ አመላካች ነጥቦች**

- በኣንድ ቤተሰብ ውስጥ ሴቶች ሃብትን የመቆጣጠር ስልጣን አለመኖር ከውሳኔ-ሰጭነት ውጭ ያደርጋቸዋል።

## 6. ታርክ ፆታዊ ጉዳዮች በተመለከት ከስነ-ጾታ ጋር የተያያዙ ታሪኮች

6.1. ቀጥሎ የተሰጠው ታሪክ አላማው በፕሮጀክቱ ለታቀፉ አርሶ አደሮች በገሀዱ አለም ያለ ታሪክ በማስረዳት ከሥርዓተ-ፆታ ስልጠናው ያገኙትን እውቀት በተግባር ካዋሉት ምን አይነት ጥቅም እንደሚያስገኝላቸው ግልጽ ስእል ለመስጠት ነው፡፡

6.1.1. ሳጥን 1 /Column1: ስለ አንድ በግብርና የሚተዳደር ቤተሰብ አባወራ ታሪክ

ከእለታት አንድ ቀን ለመሰብሰብ የደረሰ ቲማቲምየን ለመሸጥ በማሰብ በጠዋቱ ከቤት ወጥቼ ገበያ ፍላጋ ተጓዝኩኝ ፡፡ እኔ ሩቅ ገበያ ፍለጋ ላይ ስደክም አንድ ገዥ ወደ ቤቴ መጣና ሚስቴን አገኛት፡፡ ሰውየው ሚስቴን ቲማቲሙ ትሸጥለት ዘንድ ከቻለች ጠየቃት፡፡ ነገር ግን ለመሸጥ ምንም ስልጣን ስላልነበራትና የኔም እቅድም ባለማወቅዋ እንደማትችል ነገረችው፡፡



የኔው ገበያ ፍለጋ ውጤት አልባ በመሆኑ ወደ ቤቴ አመራሁኝ ፡፡ ቤት በደረስኩ ጊዜ ባለቤቴ የእለቱ ኹነቶች አወራችኝ፡፡ ባመለጠኝ እድል በጣም መጥፎ ስሜት ተሰማኝ፡፡ የደረሰ ቲማቲሜን የምሸጥበት ቦታ ባለማግኘቴ ተበላሸቶ ቀረ፡፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለስልጠናው ተሳታፊ አርሶ አደሮች ጠይቁ፡-

- ✓ በታሪኩ የሰማችሁት ሁኒታ በእናንተ ኢጋጥም ያውቃልን?
- ✓ ችግሩ የተከሰተው ለምን ይመስላቹሃል?
- ✓ ይህ አይነት ችግር እንዴት ሊቀረፍ ይችላል?

ሳጥን 2/ Column2:- ስለ አንድ በግብርና የሚተዳደር ቤተሰብ እማወራ ታሪክ

ባለቤቴ " ቀይ ሽንኩርት ትርፋማ መሆኑ ሰምቻሉሁኝ፡፡ ጠቅላላ ማሳችን ቀይ ሽንኩርት እንትከለው " ብሎ ነገረኝ፡፡ እኔ ግን አንዲህ በማለት ሀሳቡን ተቃወምኩት " አዎን እስማማለሁ ነገር ግን በግማሽ ማሳ ይሁን ፣ መላው ማሳችን አይሆንም
,

ምክንያቱም በርካታ ሌሎች አርሶ አደሮች ቀይ ሽንኩርት እንደተከሉ ኣይቻለሁ፡፡ በተጨማሪም ገና ብዙ ሰዎች ቀይ ሽንኩርት እንተክላለን ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ ምርታችን ለገበያ በምናደርሰበት ወቅት ዋጋው እንደሚቀንስ አውቃለሁ ፡፡ ባለቤቴ ግን ያልኩትን አልሰማኝም፣ ያሰበውን ብቻ አደረገ፡፡ በመጨረሻም እንደገመትኩት ከፍተኛ ኪሳራ ደረሰብን ፡፡ ከዚህ መራራ ልምድ በኋላ ግን ባለቤቴ " በዚህ ወቅት ምን ሰብል ብናመርት ጥሩ ይመስልሻል" በማለት ይጠይቀኝ ያማክረኝ ጀምሯዋል፡፡



ለስልጠናው ተሳታፊ አርሶ አደሮች ጠይቁ፡-

- ✓ ተመሳሳይ ሁኒታ በእናንተ ኢጋጥም ያውቃልን?
- ✓ ችግሩ የተከሰተው ለምን ይመስላችኋል?
- ✓ ይህ አይነት ችግር እንዴት ሊቀረፍ ይችላል ትላላችሁ?

7. የ1ኛው ቀን ማጠቃለያ

7.1. ደረጃ 5. የማጠቃለያ ክፍል

**የክፍለ ጊዜው ዓላማ**

ከስልጠና መርሃ ግብሩ ግብ አኳያ የስልጠናው ተሳታፊ አርሶ አደሮች በቂ ግንዛቤ መጨበጣቸውን ለማረጋገጥ

**የሚፈጀው ጊዜ**

15 ደቂቃ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች**

ኣያስፈልግም

**7.2.** የትግበራ ክንውን አካሄድ

| **ሂደት** | **ተግባሮች** |
|---|---|
| **ደረጃ 1** | የስልጠናው ተሳታፊ አርሶ አደሮች ከስልጠናው ምን እንደተማሩ ጥያቄ ይቀርብላቸዋል። በማስከተል በያንዳንዱ የስልጠናው ደረጃ የተዳሰሱትን ጠቃሚ ነጥቦች "አሁን ተሳታፊዎች ተረድተዋል" የተሰኘው ልምምድ በማስታወስ መረዳታቸውን ማረጋገጥ ። |
| **ደረጃ 2** | ለስልጠናው ተሳታፊ ቡድን ስለ ቀጣዩ የጾታ ድርጊት መርሀ-ግብር ማዘጋጀት ፕሮግራም የሚዘጋጅበት ቀን ማሳወቅ |
| **ደረጃ 3** | የመዝጊያ ንግግር |

8. *የሥርዐተ-ፆታ ትንታኔ መተግበርያ 4*

Preparation › 1ኛ ቀን › 2ኛ ቀን

## የድርጊት-መርሀ ግብር ማዘጋጀችት

8.1. *ደረጃ 6. የሥርዐተ-ጾታ ድርጊት-መርሀ ግብር ማዘጋጀችት*

**አላማ**

ከዚህ በፊት የሰራናቸው መልመጃዎችና የውይይት ነጥቦች ለመከለስ፡፡

በሴቶች ላይ የተጫነው ከባድ የስራ ጫና ለመቀነስ የቤተሰብ አባላትን በማሳተፍ የጾታ ምላሽ የድርጊት መርሃ-ግብር ለማዘጋጀት፡፡

**የሚፈጀው ጊዜ**

- 15 ደቂቃ ለማጠቃለል
- አንድ (1) ሰዓት የድርጊት መርሃ-ግብር ለማዘጋጀት

**የስልጠና ቁሳቁስ**

ተገላጭ ቻርት፥ ማስመሪያ ፥ መፃፊያ ማርከር

8.2. የትግበራ ክንውን አካሄድ

| ሂደት | ዋና ተግባር |
|---|---|
| ደረጃ 1 | ወደ ሁለተኛው ዙር ሥርዓተ-ፆታ ስልጠና የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር፡፡ **የስልጠናው ተሳታፊ አርሶ አደሮች ካለፈው ስልጠና የተማራሩት አንኳር ነጥቦች ማስታወስ፡፡ ለማረጋገጥ የተዳሰሱትን ጠቃሚ ነጥቦች “ አሁን ተሳታፊዎች ሁሉንም ልምምዶችን ተረድተዋል” የሚለውን ማስታወስ የተሰኘው ልምምድ በማስታወስ ፡፡** |
| ደረጃ 2 | በዚህ ክፍል ደግሞ የስልጠናው አላማ በሴቶች ላይ የተጫነው ከባድ የስራ ጫና የቤተሰብ አባላት በማሳተፍ መመቀነስ መሆኑ ማብራራት ያስፈልጋል፡፡ የበሴቶች ከባድ የስራ ጫና እንዴት መቀነስ እንደሚቻል ውይይት ማድረግ፡፡ በማስከተለል የጾታ ምላሽ የድርጊት መርሃ-ግብር በማዘጋጀት፡፡ |
| ደረጃ 3 | ከታች በተሰጠው ቅጽ “ የድርጊት መርሃ-ግብር” በመሙላት/በማዘጋጀት |

| አላማ | እጅግ አድካሚ ስራ | ተግባር | መቼ | | አስፈላጊ ሀብት | ፈጻሚ አካል | ክትትል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሴቶች ስራ ጫና መቀነስ | ውሀ መቅዳት | የተሻሻለ ምድጃ መግዛት | ግንቦት 2021 በሚቀጥለው የምርት ወቅት የአትክልት ሽያጭ ሲደርስ | | ጥሬ ገንዘብ (ብር 1,000)፣ የሰው ጉልበት ምድጃው ለመገንባት | እያንዳንዱ ተሳታፊ ቡድን | የልማት ሰራተኞች እና ቡድን መሪ |

ትክክለኛ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ

ተሳታፊዎችን ከሁሉ የበለጠ በጣም አድካሚና ጊዜ የሚፈጅ ስራ ምንድን ነው በማለት መጠየቅ

መፍትሔ ከመስጠት አንጻር- ብዙ ጉልበትና ወጭ የማይጠይቅ ተግባር እንዲጠቁሙ ማድረግ

**ቁልፍ የ ግንዛቤ/ክህሎት መፈተሻ ነጥቦች**

- የስልጠናው ተሳታፊዎች የበሴቶች ከባድ የስራ ጫና ማቃለል የሚያስችል የድጊት መርሃ-ግብር መቅረጽ ችለዋል፣
- የድጊት መርሃ-ግብሩ ለመተግበር አነስተኛ የውጭ ግብአት ብቻ ከታከለበት ትልቅ ለውጥ ማምጣት ያስችላል ።



ድህረ-ስልጠና የድጊት መርሃ-ግብር መሰረት **ቀጣይነት ያለው ክትትል ድጋፍ** መኖር የአርሶ ደሮች ባህሪያዊ ለውጥ ለማማጣት ወሳኝ ሚና አለው። ለዚህም የቀበሌ ልማት ሰራተኞችና ወረዳ ባለሙያዎች የአርሶ ደሮች መሻሻል በማስቀጠል ድጋፍ እንድያደርጉ ይበረታታሉ። የተገኙ በጎ ልምዶች በአርሶ ደሮች መካከል ልውውት ማድረግ አንዱ ከሌላው ትምህርት በመቅሰም ስነ-ጾታ ማካተትን ለመተግበር የሚያደርጉትን ጥረት ማገዝ ወሳኝ ነው፡፡